# የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ በውጭ አገር

## ክፍል ሶስት ማጠቃለያ

### ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ኅብረትን መፍጠር ይቻላል። የኢትዮጵያውያን የወቅታዊ ጉዳዮች መወያያ መድረክ 'ከረንት አፌየርስ' ን እንደምሳሌ

በክፍል ሁለት ጽሁፌ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ እንደ አንድ ሀገር ሰውነት በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በጋራ፣ እንደየሚኖሩባቸው ሀገራት ደግሞ በተለይ ሲያደርጉ በሚገቡዋቸው ጉዳዮች ዙርያ የአስተሳሰብ፣ የሀይማኖት፣ የፖለቲካ ልዩነቶች ወዘተ እንደተጠበቁ ሆነው አንድ በሚያደርጉዋቸው ጉዳዮች በማበር ጠንካራ ማሕበርን ለመፍጠር ያዳገተበትን ምክንያትና መፍትሄ አዘል ሀሳብ ለማቅረብ ሞክሬ ነበር። እንደየአካባቢያችን ጠንካራና ደካማ ማኅበራትን መለስ ብለን መመልከት እንችላለንና እጅግ በርካታ የመፍትሄና የማጠናከርያ ሀሳብ እንደችግሩ መጠንና ስፍራ በማቅረብ መሻሻልን እናመጣለን የሚል እምነት አለኝ። በዚህ መልክ መደራጀት ከተቻለ ደግሞ የአንደኛችን ማኅበር ከሌላኛው በመማር በመተጋገዝና ልምድ በመለዋወጥ ሁዋላ ቀርና እርባና ቢስ ከሆነ ንትርክና ክርክር አልፈን ፍሬያማ የሆነ ስራ ለመስራት ስለመቻላችን ማሰብ ይቻለናል። ዋናው መስራት የሚፈልገውና አፍራሹ በአግባቡ ሊለይና ከጅምሩ መፍትሄ ሊፈለግለት የመቻሉ ጉዳይ ነውና!! የመንገድ ምርጫ ሳይሆን የግብ አንድነት ሲኖር ደግሞ ሁሉም ውጤት ላይ ስለሚያተኩር የትኛውን መንገድ እንከተል የሚለው ክርክር ተስፋ አያስቆርጡትም። በመሆኑም ብዙ ውጣ ውረዶችን አልፎ ካሰበበት ይደርሳል። ብዙ ጊዜ ትኩረት የምንሰጠው መጥፎ የሆኑ ጉዳዮች ላይ በመሆኑና በግቡ ሳይሆን በመንገዱ ምርጫ ላይ በማነጣጠር ገና ጉዞ ሳንጀምር መፋረስና ተጓትተን መውደቅ ስለሆነ ብዙዎቻችን ማድረግ የምንችለውንና የኛን ድርሻ ለማየት ፋታ የለንም። በዚህ በመጨረሻው ክፍል ላይ ላቀርብ የምፈልገው ቢኖር እንኳን በአንድ ከተማ ወይም ሀገር የምንኖርና እርስ በእርስ የምንተዋወቅ ሰዎች ይቅርና የግብና የአላማ አንድነት ያስተሳሰራቸው ወገኖች በአካል ሳይተዋወቁም ተደራጅተው ታላላቅ ተግባራትን ማከናወን መቻላቸውን መግለጽና ከዚህ መማር የምንችለው ነገር ይኖራል በሚል ምሳሌ አቅርቤ ርዕሱን ለመቋጨት ነው። በድክመታችን ላይ ሳይሆን በጥንካሬያችን ላይ እናተኩር ከአፍራሽ ስሜት ይልቅ ወደገንቢው ፊታችንን እናቀናለን።

የቴክኖሎጂ ትሩፋትን መጠቀም የቻሉ ሰዎች እንደ አስተሳሰባቸውና አላማቸው በመሰባሰብ እንደየጉዞ አቅጣቸው በሚያምኑበት መንገድ ሲንቀሳቀሱ እየተመለከትን ነው። የሙያ ማኅበራት በሙያ ዘርፋቸው ይሰባሰባሉ፣ የፖለቲካ ድጋፍ ሰጪ ማኅበራት በየአገሩ ተደራጅተው ለሚያራምዱት የፖለቲካ መስመር ጉልበት ይሆኑታል። የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ግን ከሙያ ማኅበራት፣ ከፖለቲካ ድርጅቶች በላይ አገራዊ ጉዳዮችን የሚያነሳና ሁሉን የሚያሳትፍ ማዕከል ነው። ይህ ስለመቻሉ ለመናገር ያስደፈረኝ አንድ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተደራጀ ያለ የኢትዮጵያውያን ስብስብ በመኖሩ ነው። ይህ የዘመኑን የቴክኖሎጂ ትሩፋት በመጠቀም ሁሉንም አይነት ኢትዮጵያዊ ያሰባሰበ እስትንፋሱ 24 ሰዐት ሙሉ የማይቋረጥ ማኅበር ነው። የኛው ድክመትና ጥንካሬ የሚንጸባረቅበት በሀሳብ ድርና ማግ የተሸመነ በተግባር ምሰሶና ማገር የቆመ ቤት ነው። ስሙም የኢትዮጵያውያን የወቅታዊ ጉዳዮች መወያያ መድረክ ወይም በተለምዶ እንደሚጠራው ከረንት አፌየርስ ይባላል።

ይህ ብዙሀኑ በቅጽል ስም የሚጠራራበት ክፍል ከማንበብና መጻፍ እልፍ ካላለው አንስቶ ቀለም እስከጠጣው ድረስ፣ ከወጣቱ እስከ አዛውንቱ ከአፍሪካ እስከ አውሮፓ ከኤሽያ እስከ አሜሪካ ተበትኖ ያለውን ኢትዮጵያዊ ያሰባሰበ ክፍል ነው። ጨቅላና ግልብ አሳብ ከሚያቀርቡ አንስቶ እጅግ አስተዋይ፣ ቅን አሳቢና ባለመልካም አንደበት የሆኑ ሰዎች ድረስ ይታደሙበታል። በርካታ በተለያየ ጎራ የሚገኙ የፖለቲካ ሰዎች ይጋበዛሉ፣ የታሪክ ምሁርም የሳይንስ ጠቢብም የአለውን እውቀት ያካፍልበታል። መጻህፍቶች ይነበባሉ የታሪክ መዛግብት ይገላለጣሉ። አንዳንዶች የፓልቶክ ግራጁዌት እስከሚመስሉ ድረስ በአስተሳሰብ ከፍ ብለዋል። እለት በእለት እያደጉ አንደበታቸው እየተገራ አሳባቸው ቀልብን የሚስብ ሆኖአል። አይን አፋርና ፈሪ ፈጣጣና ደረቅም አሉበት። ቀና የሚመስል በማር የተለወሰ መርዝ ረጨት ማድረግ የሚሹ አጋጣሚ ሲያገኙ ደፍረስ ያደርጋሉ። ከተሰባበሩ እንግሊዝኛዎች እስከተራቀቁቱ ድረስ መድረኩን ያጨናንቁታል። አፍቃሪ ወያኔዎችም ጥቂት ቃላት ወንጭፈው ፈትለክ ይላሉ። ማቅራራትና መደንፋት፣ መራገምና መውቀስ ለውጥ የሚያመጣ የሚመስላቸው ወገኖችም አልፎ አልፎ ይንጫጫሉ። አነጋገራቸው እድሜአቸውን የማያሳብቅባቸውም እንዲሁ። እድሜው ከሀያ ያልዘለለ የሚመስል የአስራ ስምንት አመት የልጅ ልጅ ያለው መሆኑ ይነገራል። የመሳርያ ተኩስ በፊልም ብቻ ያየ የሚመስለው ሰው መድፍ አገላባጭ የነበረ ሆኖ ይገኛል። ካገሩ ሲወጣ ብቻ አውሮፕላን ላይ የተሳፈረ የሚመስለው ጀቱን

በሰማይ ሲያምዘገዝግ የነበረ ፓይለት መሆኑ ይሰማል። ጋዜጠኛው፣ ሀኪሙ፣ ጠበቃው፣ ተመራማሪው፣ ተማሪው፣ መምህሩ፣ የኔ ቢጤው ሸቃይ ሁሉ ይታደሙበታል። አንዳንዶች የተለጎመ አንደበት ይዘው ኮምፒዩተሩ አጠገብ ይቁነጠነጣሉ። ሌሎች ደግሞ ከመጋረጃው ጀርባ ትግሉን ያጧጡፋሉ፣ ተውኔቱን ያደማምቃሉ፣ ከገንዘባቸው ይቸራሉ። የማኅበሩ አባላትና ታዳሚዎች ልክ እንደ ኢትዮጵያውያን ስብስብ ሁሉ አምጡ ሳይባል ቀድመው የሚሰጡና ቃል ገብተው ድምጻቸው የሚጠፋ ስለመኖራቸውም እሰማለሁ። እንዲያም ሆኖ ግን መሬትን እንደሚሸነሽኑት የሀሳብ መስመሮች በሀሳብ መስመር የተጠላለፈ ግን በርካታው አባላት በመልክም በስምም የማይተዋወቅ ነው። አላማው እምነትን በልቡ በማስረጹ ምክንያት ገንዘብ ሲሰጥ ለእርዳታ እጁን ሲዘረጋ ለቤተክርስትያን መባ የመስጠት ያህል ከሙሉ እምነቱ ጋር ነው። በዚህም ምክንያት ማንም ሊሆን ይችላል ብሎ የማያስበውን ታላላቅ ተግባራትን አከናውኖአል። ታድያ እኒህ በአብዛኛው በዐይነ ሥጋ ያልተያዩ ሰዎች ይህን ያህል የእውቀት፣ የእድሜ፣ የልምድና የአመለካከት ልዩነት ያላቸውን ሰዎች ምንድን ነው ያስተሳሰራቸው? ልዩነታቸው እንዲህ የበዛ ሆኖ ሳለ አንድ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል።

የከረንት አፌየርስን አባላት (እድምተኞችን በጅምላው ሳይሆን) አንድ የሚያደርጉዋቸው ጥቂት ነገሮች ናቸው። እኒህ ጥቂት የሚባሉት ነገሮች ግን የአንድ ስብስብን ሕይወት ሊሰጡ ወይም ሊነሱ የሚችሉ ብልቶች ናቸው። በአገር ሕልውናና አንድነት፣ በሕዝብዋ እኩልነትና ነጻነት ላይ የማያወላውል አቋም አላቸው፣ የኢትዮጵያ መሪ ከእንድብር ይምጣ ከአሞራ ገደል፣ ከሆሮ ጉዱሩ ይምጣ ከፉኝዶ፣ ሴት ትሁን ወንድ እስላም ይሁን ክርስትያን በትረ መንግስቱን የሚጨብጠው በሕዝብ ምርጫ መሆን አለበት ብለው ያምናሉ። ይህ በሁሉም የሕዝብ ስልጣን ተዋረድ መተግበር አለበት ይላሉ። ያለይሉኝታና ፍርሀት በወያኔና በጎጠኞች ላይ የማያወላዳ አቋም አላቸው። በመድረኩም ላይ በዚህ ጉዳይ መለሳለስ ፈጽሞ አያሳዩም። ለኢትዮጵያ ሕልውና፣ ነጻነትና አንድነት የታገሉና የሚታገሉትን ሁሉ አክብሮት ይሰጣሉ፣ ይንከባከባሉ ድምጻቸው እንዲሰማም ያደርጋሉ። የኢትዮጵያን ታሪክና ባሕል የሚያስተዋውቁ ቅርስዋን ለሚንከባከቡ ሁሉ ለጀግና የሚሰጠውን ክብር ይሰጣሉ። ሕዝብን ወይም ታዳሚውን በእውቀት ማነጽና በመረጃ አቅርቦት ከወቅቱ ሁኔታ ጋር የማስኬድ ተግባርን በትጋት ይፈጽማሉ። በገንዘብ፣ በእውቀትና በመረጃ ልውውጥ ከፍተኛ ተግባራትን ያከናውናሉ። ይህ እኔ የማውቀውና የምመሰክረው ነው። የማላውቀው ግን ብዙ ነገር ሊኖር ይችላል። ይህ ነው በልዩነት መካከል ያለውን ታላቅ አንድነት፣ በመለያየት መካከል ያለውን አብሮነት ጉልበት የሚሰጠው።

ከረንት አፌየርስ የኢትዮጵያውያን የመወያያ መድረክ ነው። መወያየት ደግሞ ለተግባር ኃይል ሰጪ ነዳጁ ነው። ከመወያያ መድረክነት ወደ ማኅበርነት ያደገና ከውይይት መድረክ እልፍ ብሎ የተግባር መድረክም የሆነ ስብስብ ነው። ብዙዎች በቀላሉ ሊያደርጉ ያልቻሉትን ከኢትዮጵያውያን ጋር የመረጃ ድልድይ በመሆን የሬድዮ ጣብያ የከፈተና በአንድ ሰዐት የስርጭት ጊዜ በመረጃ የታጨቀ ማራኪና ተናፋቂ ፕሮግራምን መምራት የቻለ ነው። በርካታ ተግባራትን በማከናወን በአይነቱ የመጀመርያ የሆነ የኢትዮጵያውያን ማኅበርን ማቋቋም ችለዋል። ስለ አደረጃጀቱና ስለ ሕገ ደንቡ ስለ አባላቱም መብትና ግዴታ የማውቀው ብዙ ባይኖርም የሀሳብና የዓላማ አንድነት በመላው ዓለም ያሉትን ካሰባሰበ በከተማና በሀገር ደረጃ በአካል የሚተዋወቁ ሰዎች ጠንካራ ማኅበር ለመፍጠር ሊያዳግታቸው አይገባም እላለሁ። እኒህ በየሀገራቱ ተበትነው ያሉ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በግላቸው ወይም ከተባባሪዎቻቸው ጋር በመሆን አኩሪ ተግባራትን እየፈጸሙ መሆኑን በተከታታይ ወጤት ተኮር እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሪ ሚና ሲጫወቱ ተመልክተናል። በጽሁፌ ማቅረብ የሞከርኩት በግል የተመለከትኩትና መፍትሄ ሊሆን ይችላል ያልኩትን ሀሳቤንና ሆኖ የምናየውን ጠንካራ የኢትዮጵያውያን ስብስብ እንደምሳሌ በመጥቀስ በድክመታችን ከምንተክዝ በጥንካሬያችን ላይ ብንረባረብ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያኮራንን ተግባር መፈጸም እንችላለን የሚለውን እምነቴን ለመግለጽ ነው። ጠንካራ ማኅበር መፍጠር ችለናል የሚሉ ደግሞ ያላቸውን ቢያካፍሉ ልምድ ለመለዋወጥ ይረዳልና የእውቀት ቅብብሎሹን እንቀጥል። ከእውቀት ማነስና ከልምድ ማጠር ምክንያት የሳትኩት ወይም የተሳሳትኩት ካለ ከአስተያየታችሁ ልማር ዝግጁ ነኝ።

## እግዚአብሄር ትዕግስትና መቻቻልን ይስጠን!!

ዳኛቸው ቢያድግልኝ
biyadegelgne@hotmail.com